United Way of King County

King County

# ኪንግ ካውንቲ የምግብ ዋስትና እገዛ ፕሮግራም
# ለማመልከቻዎች የቀረበ ጥሪ | ቀነ-ገደብ ዲሴምበር 8፣ 2021

## I. መነሻ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ በፑጌት ሳውንድ የምግብ ዋስትና እጦት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። እ.ኤ.አ. በ2020፣ ችግሩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በነበረበት ወቅት፣ የምግብ ዋስትና እጦትን ሪፖርት ያደርጉ የነበሩ የኪንግ ካውንቲ ቤተሰቦች ቁጥር በእጥፍ ጨምሯል፣ እና የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች የምግብ ዋስትና እጥረት መጠን ከወረርሽኙ ማብቂያ በኋላም ሊቀጥል እንደሚችል ይገምታሉ።

በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ እና በዋሽንግተን ስቴት ዩኒቨርሲቲ የተደረገ ጥናት በክፍለ ሃገርም ሆነ በኪንግ ካውንቲ ውስጥ በምግብ ዋስትና ላይ ከፍተኛ ልዩነቶች እንዳሉ ያሳያል፣ ባለዝቅተኛ ገቢ ቤተሰቦች፣ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች እና ጥቁሮች ወይም ቅለመ-ነጭ ያልሆኑ ሰዎች ባልተመጣጠነ ሁኔታ ረሃብ ያጋጥማቸዋል። ጠንካራ የትስስር መረብ ያላቸው ድርጅቶች ደንበኞቻቸው የፌዴራል የምግብ ዕርዳታ ፕሮግራሞችን እና የአደጋ ጊዜ የምግብ ሥርዓትን እንዲያገኙ የሚደግፉ ቢሆንም፣ ተለይተው የታወቁ የምግብ ተደራሽነት ክፍተቶች አሁንም እንደቀጠሉ ነው፣ በተለይም በኮቪድ-19 ምክንያት ያልተመጣጠነ ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች ተጽዕኖዎች በደረሰባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ።

እነዚህን የምግብ ተደራሽነት ክፍተቶች ለመቅረፍ፣ በምግብ ዋስትና እገዛ ፕሮግራም መኩል $4,400,000 የፌዴራል ፈንድን ለማደል ከህዝብ ጤና ጥበቃ - ሲያትል ጋር አጋርነትን ፈጥሯል። ይህ የገንዘብ ድጋፍ ለኪንግ ካውንቲ የተመደበው በኮሮና ቫይረስ የአካባቢ የገቢዎች/ፊስካል ማገገሚያ የገንዘብ ድጎማ በኩል ሲሆን፣ ይህም በአሜሪካው ከአደጋ አድን ዕቅድ ድንጋጌ አካል ነው። የዩኤስ ግምጃ ቤት ለእነዚህ ገንዘቦች ተፈቃጅ አጠቃቀሞች ላይ የፌዴራል መመሪያ ያወጣ ሲሆን፣ ኪንግ ካውንቲም ለዩናይትድ ዌይ ተጨማሪ መመሪያ እና ገደቦችን ሰጥቷል። የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮግራም ቀመር/ዲዛይን በ2020 እና 2021 በህዝብ ጤና - ሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ በሚመራ የማህበረሰብ ተሳትፎ ሂደት መረጃ ቀርቦለታል።

## II. የፕሮግራም ዓላማ

የኪንግ ካውንቲ የምግብ ዋስትና እገዛ ፕሮግራም ዓላማ በኮቪድ-19 ምክንያት ያልተመጣጠነ ተጽዕኖ ለደረሰባቸው የደቀቀ ኢኮኖሚያዊ አኗኗር ውስጥ ለሚኖሩ ማህበረሰቦች ባህላዊ ተስማሚነት እና የተለየ የአመጋገብ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ አቅርቦቶች ተደራሽነትን ከፍ ለማድረግ ነው። በምግብ ዋስትና እገዛ ፕሮግራም በኩል የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ፣ በኪንግ ካውንቲ የሚታዩ እና ተለይተው የሚታወቁ የምግብ ተደራሽነት ክፍተቶችን የሚቀርፉ ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል ወይም ለማስፋት የታለመ ነው።

በዚህ ፕሮግራም በኩል፣ የኪንግ ካውንው ዩናይትድ ዌይ ከማህበረሰብ-አቀፍ ድርጅቶች፣ ከምግብ ፕሮግራሞች፣ ከምግብ ባንኮች/የምግብ ቋቶች፣ ለተደራሽነት ዝቅተኛ-መሰናከል ከሆኑ እና ቢያንስ ለ12 ወራት በቀጣይነት ከሰሩ ከንድ ወይም በላይ የምግብ ፕሮግራሞች ጥምረቶች ጋር ውል ያደርጋል። ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል:

- **የምግብ ሸቀጦችን** እስከቤት ድረስ በማድረስ፣ ወደምግብ ማደያ ቦታዎች ብቅ-ብሎ በመውሰድ፣ ወይም በምግብ ባንኮች/በምግብ ቋቶች በኩል ማደል
- ***ለመብላት የተዘጋጁ ምግቦችን*** እስከቤት ድረስ በማድረስ፣ ወይም በአንስተሀ-ሂድ ዝግጅ ምግቦች ፕሮግራሞች በኩል በማዳረስ

ድርጅቶች ከተደጎሙት/ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ 75%ን ለምግብ ማዋል ይጠበቅባቸዋል። ቢበዛ 25% የሚሆነው የተደጎመው ገንዘብ ለደሞዝ፣ ለጥቅማጥቅሞች፣ ለአቅርቦቶች፣ እና ቀጥተኛ ላልሆኑ ወጪዎች ሊውል ይችላል። በዚህ ፕሮግራም ስር፣ የስጦታ ካርዶችን፣ የምግብ ቫውቸሮችን እና/ወይም መሳሪያዎችን (ማቀዝቀዣዎችን፣ የበረዶ መስሪያ ማቀዝቀዣዎችን፣ ተሽከርካሪዎችን፣ ለማከማቻ ክፍሎችን፣ ወዘተ) መግዛት አይፈቀድም። የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮግራም

ለአስተዳደር አቅም ግንባታ፣ ለካፒታል ፕሮጀክቶች፣ ለፍላጎት ግምገማዎች ወይም ለዕድ ማውጫ ፕሮጀክቶች ገንዘብ ሊመድብ **አይችልም።**

**ገንዘብ የሚመደበው/የሚሰጠው በሚከተሉት ምድቦች ስር ነው:**

**<u>ምድብ 1: የተናጠል ድርጅቶች</u>**

ይህ ምድብ በኮቪድ-19 ምክንያት ያልተመጣጠነ ጉዳት ለደረሰባቸው ማህበረሰቦች፣ ባህላዊ እና የአመጋገብ ተቀባይነት እና ተስማሚነት ያላቸው የምግብ አቅርቦትን ተደራሽነትን በማሳደግ ላይ ለሚያተኩሩ የማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ክፍት ነው።

የኪንግ ካውንቲ ዩናይትድ ዌይ ምግብን ለ... ከሚያከፋፍሉ/ከሚያድሉ ድርጅቶች ጋር የኩንትራት ውል ይዋዋላል:

- በአካባቢያዊው የአስቸኳይ ምግብ ስርዓት እና/ወይም አሁን ባለው አስተዳደር እና በፌዴራል የምግ ዕገዛ ፕሮግራሞች በኩል በቂው አገልግሎቶችን ያላገኙ የህዝብ ክፍሎች፣ ይህም በUniversity of Washington and Washington State University WAFOOD study ተለይተው የተመላከቱ የህዝብ ክፍሎችን ይጨምራል።
- ለክልል እና ለፌዴራል የምግብ ዕገዛ ፕሮግራሞች ብቁነት የሌላቸው የህዝብ ክፍሎች
- የምግብ ተደራሽነት ክፍተት እንዳለባቸው በተለዩ ክልሎች የሚኖሩ በኢኮኖሚ የተጎዱ ሰዎችን የሚያገለግሉ ፕሮጀክቶች።

በዚህ ምድብ ስር የሚደጎሙ ድርጅቶች የሚከተለውን ማሳየት አለባቸው:

- የማህበረሰብ አባላትን የማሳተፍ ታሪክ እና የማህበረሰብ ግብረ-መልስን የማመንጨት እና ምላሽም የስጠት ብቃት
- ባህላዊ ተቀባይነት ወይም ለተልየ አመጋገብ ተፈላጊነት ያላቸው፣ የተገዙ ወይም የተለገሱ ምግቦች አያያዝ/አስተዳደር ልምድ
- በባለዝቅተኛ-መሰናክል ዘዴዎች ያለማቋረጥ በቀጣይነት ምግብን የማደል/የማዳረስ ልምድ
- ተሳታፊዎቻቸው በኮቪድ-19 ምክንያት እንዴት ባልተመጣጠነ ሁኔታ ችግር/ተጽዕኖ የደረሰባቸው ስለመሆኑ ግልጽ ግንዛቤ

ዩናይትድ ዌይ ከ$150,000 እስከ $250,000 የሚደርስ የገንዘብ ድጎማ በማድረግ ከ20 እስከ 25 ድርጅቶችን በገንዘብ ይደግፋል። በኪንግ ካውንቲ ውስጥ በምግብ ዋስትኛ አለመኖር ምክንያት እጅጉን የተጎዱ የህዝብ አካላትን በጋራ የሚያገለግሉ ድርጅቶችን ስራ/ፖርትፎሊዮ ቀጣይነት ለማረጋገጥ፣ ዩናይትድ ዌይ ቢያንስ ለሚከተሉ የገንዘብ ድጎማ ለማቅረብ ጥረት ያደርጋል:

- በሰሜን ኪንግ ካውንቲ ውስጥ ምግብ ለሚያከፋለው 1 ድርጅት
- ምስራቅ ኪንግ ካውንቲ ውስጥ ምግብ ለሚያከፋፍሉ 2 ድርጅቶች
- በሲያትል ከተማ ውስጥ ምግብ ለሚያከፋፍሉ 5 ድርጅቶች
- ደቡብ ኪንግ ካውንቲ እና ባልተጣመረው ኪንግ ካውንቲ ውስጥ ምግብ ለሚያከፋፍሉ 7 ድርጅቶች

**ምድብ 2: ጥምረቶች**

ይህ ምድብ በኮቪድ-19 ምክንያት በከፍተኛ መጠን ያልተመጣጠነ ተጽእኖ ለደረሰባቸው ወገኖች ድራሽ አገልግሎትን ለማቅረብ ልዩ ወይም አዲስ የስርጭት ሞዴሎችን የሚጠቀሙ ጥምረቶችን ለመደገፍ የታለመ ነው። ይህም፣ መጠነ ሰፊ አቅርቦቶችን እስከቤት ድረስ የማድረስ ፕሮግራሞችን፣ የአመጋገብ ተፈላጊነት ወይም እንደየባህሉ ተቀባይነት ያላቸው የምግብ ሸቀጦችን ወይም የተሰናዱ ምግቦችን በጅምላ መግዛትን፣ እና/ወይም በድንገት ደራሽ ምግብ አቅራቢዎች እና በማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች መካከል ያለውን የትብብር ሽርክና ሊያካትት ይችላል።

የኪንግ ካውንቲው ዩናይትድ ዌይ፣ ከሚከተሉት መመዘኛዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ ሆነው በኮቪድ-19 ምክንያት ያልተመጣጠነ ተጽዕኖ ለደረሰባቸው ህዝቦችን በማገልገል ላይ ያሉ ጥምረቶችን ይደግፋል:

- በደቡብ ሲያትል፣ በደቡብ ኪንግ ካውንቲ እና በኪንግ ካውንቲ ገጠር እና በካውንቲው ያልተጠቃለሉ አካባቢዎችን ጨምሮ፣ ነገር ግን ወሰኑ በዚህ ብቻ ሳይገደብ፣ የምግብ ተደራሽነት ክፍተት ባለባቸው ክልሎች ውስጥ በኢኮኒ ለተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚያገለግሉ ፕሮጀክቶች።
- የተለያዩ የባህላዊ ምግቦች ልምድ/ፍልስጎት ያልቸው የባለብዙ ባህል ስብጥር ህዝቦች።
- የተለየ የአመጋገብ ገደብ ያላቸው ማህበረሰቦች።

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሆነው የተመሰረቱ የድርጅቶች ጥምረቶች፣ የሚከተሉትን በግልጽ የሚያሳዩ ከሆኑ እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ:

- የምግብን ፕሮግራምን በማቀድ እና ማደራጀት ላይ እንደ ጥምረት አብሮ የመስራት ልምድ
- ምግብ ተደራሽነት ክፍተቶችን ለመፍታት በስርአት ደረጃ የመስራት ልምድ
- የማህበረሰቡን አስተያየት የማመንጨት እና ምላሽ የመስጠት ፈቃደኛነት እና ችሎታ
- በዝቅተኛ-መሰናክል ደረጃ ምግብን ለተጠቃሚዎች የማድረስ ልምድ ማስረጃ
- ለአመጋገብ የተለዩ እና እንደየባህሉ የተለዩ የሆኑ ምግቦችን በደረጃው ልክ የማቅረብ ልምድ
- ባህላዊ ተቀባይነት ወይም ለተልየ አመጋገብ ተፈላጊነት ያላቸው፣ የተገዙ ወይም የተለገሱ ምግቦች አያያዝ/አስተዳደር ልምድ
- ከፍተኛ መጠን ያለው ምግብን ገዝቶ የማዳረስ/ማደል ብቃት ወይም ችሎታ ($30,000 እስከ $40,000 የሚደርስ ዋጋ ያለውን ምግብ፣ በኮንትራቱ ጊዜ ውስጥ በየወሩ ገዝቶ ማቅረብ)

ዩናይትድ ዌይ እስከ አራት ለሚደርሱ ጥምረቶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይህም ለእያንዳንዱ ተደጓሚ የጥምረቱ አባል ድርጅት ከ$500,000 የማይበልጥ ድጎማ ያደርጋል። ተናጠል የቅንጅት አባላትም በምድብ 1 (የተናጠል ድትጅቶች) በሚለው በኩል በተናጠል ማመልከት ይችላሉ፣ ይህም የሚቻለው፣ ማመልከቻቸው በጋር አሰራር ላይ ለሚከወን ስራ ከሚመደበው ገንዘብ በተለየ ሁኔታ ራሱን የቻለ የስራ አካል ሆኖ የቀረበ እንደሆነ ነው።

ዩናይትድ ዌይ የገንዘብ ድጎማውን የሚሰጠው በኢኮኖሚ የደቀቁ ማህበረሰቦችን/ሰዎችን  ወይም ለድጎማው በዝቅተኛው ደርጃ ላይ ያሉ ስርዓቶችን ፍላጎቶችን በሚያስቀድም መልኩ ሲሆን፣ ይህን ስራ ለመተግበርም ኮንትራትን ለመዋዋል የሚያልመው/የሚፈልገው ይህንኑ መልከዓ-ምድራዊ ክልሉን እና በኪንግ ካውንቲ ውስጥ በምግብ ዋስትና እጥረት በከፍተኛ ደረጃ የተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለማገልገል በጋራ ጥምረት ሊሰሩ ከሚችሉ የስራ የፖርትፎሊዮ ጥምረቶች ጋር ነው።

## III. ገንዘባዊ ድጎማው እና ጊዜው

የምግብ ዋስትና ድጋፍ/ዕገዛ ፕሮግራም፣ በፌዴራል የአሜሪካ የግብዓት ዕቅድ ድንጋጌ መሰረት፣ ለማህበረሰብ-ተኮር ድርጅቶ፣ ለተሰናዶ ምግቦች ፕሮግራሞች፣ ለምግብ ባንኮች/ለምግብ ቋቶች፣ እና ለጥምረቶች/ቅንጅቶች የ$4,400,000 ድጎማ ያደርጋል። እዚህ ላይ ልብ ይበሉ፣ ተደጓሚ ፕሮጀክቶች ተመሳሳይ የባጀት መጠን ላይኖራቸው ይችላል፣ እንደዚሁም አንዳንድ አመልካቾች ከሚፈቀድላቸው የድጎማ መጠን ገሚሱ ብቻ ለሰጣቸው ይችሉ ይሆናል።

የኮንትራክቱ ጊዜ ርዝማኔም ከጃንዋሪ 15 ቀን 2022 እስከ ኦክቶበር 31 ቀን 2022 ድረስ ይሆናል።

## IV. ማን ማመልከት እንደሚችል:

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት በቀጣይነት ተከታታይ የምግብ ማዳረስ ዕቅድ እና ፕሮግራምን ሲያቀርቡ ከነበሩ ኤጀንሲዎች፣ ጥምረቶች እና ሽርክናዎች፤ ከፍተኛ መጠን ያለው ምግብ በመደበኛነት የማከፋፈል አቅም ያላቸው እና የሚከተሉትን ማድረግ ከሚችሉ ሁሉ የሚመጡ ማመልከቻዎችን እናበረታታለን፡

-  ነባር የምግብ ፕሮግራሞችን ወይም ስርዓቶችን ጠብቆ ማቆየት ወይከ ማሳደግ የሚችሉ።
-  የተመደበላቸውን ገንዘባዊ ድጎማ በጃንዋሪ 15 ቀን 2022 እና ኦክቶበር 31 ቀን 2022 መካከል ጥቅም ላይ የሚያውሉ።
-  ከተሰጠው የገንዘብ ድጎማ ውስጥ ቢያንስ 75%ን ለምግብ የሚያውሉ። ቢበዛ 25% የሚሆነው የተደጎመው ገንዘብ ለደሞዝ፣ ለጥቅማጥቅሞች፣ ለአቅርቦቶች፣ እና ቀጥተኛ ላልሆኑ ወጪዎች ሊውል ይችላል።
-  የምግብ ዋስትና እገዛ ፕሮግራም ገንዘባዊ ድጎማዎችን **ሁሉ** ኪንግ በዋሽንግየን፣ ካውንቲ ውስጥ ለሚኖሩ/ለሚሰሩ ሰዎች በቀጥታ ለሚያደርሱ።
-  ለመግብ ሸቀጦች እና/ወይም ለተዘጋጁ ምግቦች ቀጣይነት ያለው ተደራሽነትን ለሚያቀርቡ:
    - ምግብ-ነክ ሸቀጦችን የሚያከፋፍሉ ፕሮግራሞች ለማህበረሰቡ አባላት በየወሩ ቢያንስ ሁለት ስርጭቶችን እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው።
    - የተዘጋጁ ምግቦችን የሚያከፋፍሉ ፕሮግራሞች በየሳምንቱ ቢያንስ ሶስት ዝግጁ ምግቦችን ተደራሽ ማድረግ አለባቸው።
-  በክፍል V ላይ የተዘረዘረውን መስፈርት ለሚያሟሉ።

**ፕሮግራሞች የምግብ ዋስትና እገዛ ፕሮግራም ፈንድን ለሚከተሉ ነገሮች መጠቀም አይችሉም:**

-  ለአስተዳደር ብቃት ግንባታ
-  ለካፒታል ፕሮጀክቶች
-  ለፍላጎቶች ግምገማዎች
-  ፕሮጀክቶችን ለማቀድ
-  የስጦታ ካርዶችን ለመግዛት
-  የምግብ ቫውቸሮችን ለመስጠት
-  መሳሪያዎችን ለመግዛት (ማቀዝቀዣዎ (ፍሪጅ)፣ በረዶ የሚሰሩ ማቀዝቀዣዎች፣ ተዝከርካሪዎች፣ የማከማቻ ክፍሎች (መጋዘኖች)፣ ወዘተ.)

## V. የብቁነት መስፈርቶች

አመልካቾች፣ በምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮግራም በኩል የሚደረገውን የፌደራል ድጎማ (ፈንዲንግ) ማግኘት ይችሉ ዘንድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው:

### A. የገንዘብ አቅሙ ያለበት ደረጃ/ሁኔታ: ኤጀንሲዎች፣ አንድም:

- በዋሽንግተን ግዛት/ስቴት ውስጥ፣ እንደ አትራፊ ያልሆነ የግል ድርጅት የትቋቋሙ እና የፌደራል 501(c)(3) ደረጃ/ሁኔታ ያላቸው መሆን አለባቸው። የአመልካቹ የ 501(c)(3) ደረጃ በጥሩ አቋም ላይ ያለ መሆን መሆን አለበት፣ እናም ባለፈው ዓመት ያልተሻረ መሆን አለበት።

- የ501(c)(3) ደረጃ ያለው የገንዘባዊ ጉዳዮች (ፊስካል) ደጋፊ (ስፖንሰር) ያለው መሆን እና በምግብ ዋስትና እገዛ ስር የተሰጠውን ገንዘብ በአግባቡ ጠብቆ ስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ዋስትና የሚሆን በቂ እና አመርቂ የአስተዳደር እና የሂሳብ አያያዝ ስርዓቶች ያቀናጀ የአሰራር ብቃት የላእው መሆኑን በተግባር ያስየ መሆን
- በ RCW 35.21.660 ወይም RCW 35.21.7301 መሰረት የተቋቋመ የህዝብ ኮርፖሬሽን፣ ኮሚሽን፣ ወይም ባለስልጣን መሆን። የአመልካቹ ህጋዊ ሰውነት ሁኔታም በጥሩ አቋም ላይ መሆን አለበት፣ እናም ቀደም ሲል በነበረው ዓመት ያልተሻረ መሆን አለበት።

B. **የSAM ምዝገባ**: የገንዘብ ድጎማ የሚደረግልቸው ኤጀንሲዎች የፌደራል ስርዓት ለድጎማ አስተዳደር (SAM) ውስጥ በወቅቱ ተመዝግበው የሚገኙ መሆን ይፈለግባቸዋል። ለድጎማ ጥያቄ ለማመልከት የSAM ምዝገባ የማይጠየቅ ቢሆንም፣ ድጎማው የተደረገላቸው ኤጀንሲዎች ግን በ15 ቀን 2022 ላይ ወቅታዊ የSAM ምዝገባ እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል። ለSAM ለማመልከት፣ sam.gov ን ይጎብኙ።

C. **የደንበኛ አገልግሎቶች እና የሰነድ አያያዝ (ዶኪዩሜንቴዝን)**: የኮንትራት ውል የተዋዋሉ ሁሉም ኤጀምሲዎች አገልግሎቶቻቸውን በባለዝቅተኛ-መሰናክል ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅባቸውል። ለምሳሌም እንደዚህ:
- እጀንሲዎች፣ በምግብ ዋስትና እገዛ ፕሮግራም በኩል የሚደጎሙ ፕሮጀክቶን ተደራሽነት ከሚጠይቁ ማንኛውም የማህበረሰብ አባል መታወቂያ ወይም የኗሪነት ማረጋገጫ፣ የገቢ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ ወይም የዜግነት ሁኔታ መጠየቅ የለባቸውም።
- የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮግራም ግብዓቶችን ለማግኘት የሚደረጉ በራስ-መስካሪነት የሚገሩ የቤተሰብ ብዛት፣ አድራሻ፣ የገቢ ሁኔታ፣ እና ፍላጎት ለሁሉምም የማህበረሰቡ አባላት መፈቀድ አለበት።
- በራስ-መስካሪነት ተነስተው ኪንግ ካዊንቲ ውስጥ እንደሚኖሩ እና ምግብ እንደሚፈልጉ ለተናገሩ የማህበረሰ አባላት፣ ኤጀንሲዎች አገልግሎቶችን መንፈግ የለባቸውም።

የገንዘብ ድጎማ የሚቀበሉ ድርጅቶች፣ በዘር፣ በጎሳ ማንነት፣ በጾታ፣ በጾታ ምንነት፣ በሀይማኖት፣ ወይም በብሄር መሰረት ላይ ያተኮረ ልዩነት ወይም መድሎ ሳያደርጉ አገልግሎቶቻቸውን ለሁሉም ግለሰቦች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

D. **ድርጅታዊ አቅም:** ድጎማውን የሚያገኙ ኤጀንሲዎች ከፍተኛ መጠን ያለው የምግብ ስርጭትን ለማስተዳደር የሚያስችል ግብዓት ሊኖራቸው ይገባል፣ እነዚህም ነባር ሰራተኞችን፣ የምግብ ማከማቻን፣ የማጓጓዣ ግብዓቶችን፣ የግዥ ሽርክናዎችን እና ከማህበረሰብ አባላት ጋር ታማኝ ግንኙነቶችን ጨምሮ ማለት ነው። እንደዚሁም ኤጀንሲዎች ለምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮግራም ተደጓሚ ገንዘብን ከሌሎች ድርጅታዊ ወጪዎች የሚለይ የሂሳብ አያያዝን/ አሰራርን ጨምሮ፣ የፌዴራል ፋይናንስን የማስተዳደር አስተዳደራዊ አቅም ሊኖራቸው ይገባል። በገንዘብ የተደገፉ ኤጀንሲዎች የገቢ እና ወጪዎች፣ የጊዜ እና የጥረት ሰነዶች፣ እና በየወሩ የሚከፈሉ ክፍያቸው የተጠናቀቁ የሂሳብ መጠየቂያዎችን እና ደረሰኞችን የሚያሳይ የተብራራ አጠቃላይ የሂሳብ መዝገብን ጨምሮ ወርሃዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል።

E. **በኢኮኖሚ ለተጎዱ ማህበረሰቦች ማከፋፈል:** የኪንግ ካውንቲ የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮግራም አላማ በኮቪድ-19 ምክንያት ያልተመጣጠነ ተጽዕኖ ደርሶባቸው ኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ ላሉ ማህበረሰቦች፣ ባህላዊ ተቀባይነት ያላቸውን እና የተለየ የአመጋገብ ስርዓት/ገደብ ያለባቸው ሰዎች ሊመገቧቸው የሚገቡ ምግቦችን ተደራሽነት ከፍ ማድረግ ነው። በኢኮኖሚ የተጎዱ ማህበረሰቦች ማለት፣ አንድም 50 በመቶ የሚሆኑት ቤተሰቦች/አባወራዎች፣ ከአካባቢው አማካይ ጠቅላላ ገቢ ጋር ሲነጻጸር፣ ገቢያቸው ከ60 በመቶ በታች የሆኑ፣ ወይም 25 በመቶው ቤተሰቦች/አባወራዎች ከፌዴራል የድህነት መስመር በታች የሆነ ገቢ ያላቸው ማህበረሰቦች ማለት ነው። አመልካቾች ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ለመሆን ከሚከተሉት **አንዱን ወይም ከዚያ በላይ** መመዘኛዎችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡

- **የአመልካቹ የምግብ ማከፋፈያ አገልግሎቶች የሚቀርቡት በማህበረሰቡ በግልጽ በሚታወቁ አነስተኛ ሰፈሮች/ቦታዎች ላይ ነው።** ኪንግ ካውንቲ ውስጥ በህዝብ አሰፋፈር ታዋቂነት ያላቸውን እነዚህን አነስተኛ ቦታዎች ለይቶ ለማግኘት፣ የ ዩ.ኤስ. የቤቶች እና ከተማ ልማት መስተጋብራዊ የበይነመረብ ካርታን (interactive online map)ን ይጠቀሙ። ከላይ በስተግራ በኩል ሰማያዊው አሞሌ ላይ አድራሻ ያስገቡ፣ ከዚያም "Color QCT Qualified Tracts" እና “Show Tracts Outline” ላይ ጠቅ ያድርጉ፣ ከዚያም 2021ን ይምረጡ። ለባለብዙ-ቦታዎች ፕሮጀክቶች፣ ድርጅቶች አብዛኞዎቹ የመረጧቸው ቦታዎች በህዝብ አሰፋፈር መስፈርት ብቁ ታዋቂነት ያላቸው ቦታዎች ውስጥ መገኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

- **ከአመልካቹ የምግብ ስርጪት/ዕደላ መድረስ የሚችሉት ከ50% በላይ ደንበኞች የሚኖሩት በነዚህ በተመረጡት በህዝብ አሰፋፈር በሚታወቁት ከባቢዎች ውስጥ ነው።** ኪንግ ካውንቲ ውስጥ በህዝብ አሰፋፈር ታዋቂነት ያላቸውን እነዚህን አነስተኛ ቦታዎች ለይቶ ለማግኘት፣ የ ዩ.ኤስ. የቤቶች እና ከተማ ልማት መስተጋብራዊ የበይነመረብ ካርታን (interactive online map)ን ይጠቀሙ። ከላይ በስተግራ በኩል ሰማያዊው አሞሌ ላይ አድራሻ ያስገቡ፣ ከዚያም "Color QCT Qualified Tracts" እና “Show Tracts Outline” ላይ ጠቅ ያድርጉ፣ ከዚያም 2021ን ይምረጡ። ደንበኞች በራሳቸው ፍላጎት ስለመኖሪያ አድራሻቸው የቃል-መስካሪነት ሊሰጡ ይችላሉ፣ ነገርግን ግብዓቶችን ለማግኘት የኗሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም።

- **የአመልካቹ የምግብ ዕደላ/ስርጪት አገልግሎቶች በዋናነት የታለሙት ለባለዝቅተኛ ገቢ ደንበኞች ነው።** ደንበኞች በራሳቸው ፍላጎት ስለገቢያቸው የቃል-መስካሪነት ሊሰጡ ይችላሉ፣ ነገርግን ግብዓቶችን ለማግኘት የገቢ ማረጋገጫ ማቅረብ አይጠበቅባቸው።

VI. **የደረጃ አመዳደብ መስፈርቶች:** ማመልከቻዎች የሚመዘዘኑት እና በደረጃ የሚመደቡት የሚከተሉትን መመዘኛዎች/መስፈርቶች በመጠቀም ነው:

| **መስፈርት** | **ክብደት** |
|---|---|
| ፕሮጀክቱ በኮቪድ-19 ምክንያት ያልተመጣጠነ ተጵዕኖ የደረሰባቸው በመሆኑ በኢኮኖሚው ለተጎዱ ማህበረሰቦች ቅድሚያ ይሰጣል | 25% |
| ፕሮጀክቱ ለተገልጋዩ ማህበረሰብ በአነስተኛ-መሰናክል እና በቀጣይነት የምግብ ተደራሽነትን ያቀርባል፣ እናም ባህላዊ ተቀባይነት ወይም የአመጋገብ ተፈላጊነት ያላቸውን ምግቦች ገዝቶ የማቅረብ ልምድ አለው | 30% |
| አመልካቹ ማግብን የማከፋፈል ልምድ ያለው መሆኑን፣ እና በኮንትራቱ ጊዜ ውስጥ ምግብን በቀጣይነት እና በቋሚነት ለማደል የሚያስችል ድርጅታዊ አሳይቷል አቅም እንዳለው አሳይቷል | 20% |
| አመልካች የማህበረሰብ ግብረ-መልስን የማነቃቃት/የማመንጨት እና ምልሽ የመስጠት ችሎታን ያሳያል | 10% |

| | |
|---|---|
| አመልካች የአስተዳደራዊ አቅም እና ወጪዎችን ተከታትሎ በመያዝ ሰነዶችን በአግባቡ ሰንዶ የማስቀመጥ ልምድ እና የእርዳታ/ድጎማ ተገዢነትን የማክበር ብቃት አለው | 15% |

ዩናይትድ ዌይ የገንዘብ ድጋፍ ውሳኔን ለማሳወቅ ከበጎ ፈቃደኞች ግምገማ ኮሚቴ ጋር የሚሰራ ሲሆን፣ የገንዘባዊ ድጎማ ውሳኔንም ከህዝብ ጤአና-ሲያትል እና ከኪንግ ካውንቲ የስራ ባልደረቦች ጋር በመተባበር ያደርጋል። ዩናይትድ ዌይ እና የህዝብ ጤና - የሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ የሚቀበሏቸውን ማንኛውንም እና ሁሉንም ማመልከቻዎች ያለምንም ቅጣት ውድቅ የማድረግ መብታቸው የተጠበቀ ነው። የመጨረሻው የኤጀንሲዎች ምርጫ በዩናይትድ ዌይ እና በሕዝብ ጤና - በሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ አስተያየት ከደረጃ ኮሚቴው የተሰጠውን ሁሉንም ምላሾች ከገመገሙ በኋላ በዚህ የማመልከቻ ጥያቄ ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች በተሻለ ሁኔታ የሚያሟሉ እና በኪንግ ካውንቲ ውስጥ በኢኮኖሚ የተጎዱ ማህበረሰቦች ፍላጎቶችን ለማሟላት በጥሩ ደረጃ ላይ ያሉ መሆን አለባቸው።

## VII. ሪፖርት የማቅረብ መስፈርቶች

በምግብ ዋስትና የእገዛ ፕሮግራም በኩል የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው ኤጀንሲዎች የሚከተሉትን የሚያካትቱ መደበኛ ወርሃዊ ሪፖርቶችን በኢሜል እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል:

- አገልግሎቱ በተፈጸመበት ወር ውስጥ የተፈጸሙ የምግብ ግዢዎችን፣ ጊዜን እና የተደረጉ ጥረቶችን የሚያሳዩ ሰነዶችን፣ እና የተጠናቀቁ የክፍያ መጠየቂያዎችን (እንቮኢሶችን) ሁሉ በማጠቃለል ወጪ እና ገቢን ዘዘር አድርጎ የሚያሳይ የሂሳብ መያዣ መዝገብ (ሌጀር)።
- አገልግሎቱ በተሰጠበት ወር ውስጥ የተስተናገዱ የምግብ ዕደላዎችን/ስርጪቶችን ዝርዝ፣ በእያንዳንዱ የስርጪት ወቅት የተስተናገዱ ግለሰብ ሰዎችን ቁጥር፣ እና የተሰራጨውን የምግብ መጠን በዝርዝር የሚያሳይ የየዕለት ማከፋፈያ መዝገብ (ሎግ ቡክ)
- የሚገኝ በሚሆንበት ልክ፣ ከተገልጋይ ደንበኞች በፈቃደኝነት የተሰበሰበ፣ ግልጋሎቱ ስለተደረገላቸው ህዝቦች መረጃ። የሚጠየቀው የህዝብ መረጃ/ዳታ፣ ጎሳን/ብሄርን፣ የቤተሰብ/አባወራ ብዛትን፣ የመኖሪያ ቤት ሁኔታን፣ እና ቤተሰቡ ውስጥ ሕጻናት ልጆች እና/ወይም አረጋዊያን መኖር-አለመኖርን የሚመለከቱ መረጃዎችን ያጠቃልላል።

በኮንትራት ዘመናቸው ውስጥ፣ ኤጀንሲዎች አገልግሎቶችን እና የተሰጡ ምግቦችን፣ የፕሮግራም ስኬቶችን፣ ተግዳሮቶችን እና ቢያንስ ሁለት የደንበኛ የስኬት ታሪኮችን የሚያካትቱ አጭር የሩብ አመት ትረካ ሪፖርቶችን እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል።

## VIII. አስፈላጊ ቀኖች

ለምግብ ዋስትና የዕገዛ ፕሮጋራም አመልካቾች የሚከተሉትን ቀልፍ ቀኖች ማስታወ አለባቸው:

- **ኖቬምበር 10 ቀን፣ 2021:** ማመልከቻ ማቀረብ ክፍት ይደረጋል
- **ዲሴምበር 8ቀን፣ 2021:** የማመልከቻ ማቅረቢያ ማብቂያ ቀነ-ገደብ
- **ጃንዋሪ 10 ቀን፣ 2021:** የአሸናፊዎች ማሳወቂያ
- **ጃንዋሪ 15 ቀን፣ 2022 – ኦክቶበር 31 ቀን 2022:** የኮንትራት ዘመን

## IX. የመረጃ ክፍለጊዜ እና ቴክኒካዊ እገዛ

የማመልከቻ መረጃ ክፍለ ጊዜዎች በሚቀጥሉት ቀናት ይስተናገዳሉ። የስፓኝ ትርጉም በሁሉም የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች ላይ በቀጥታ ይገኛል።

- ኖቬምበር 15 ቀን፣ 10 a.m. | Link to Register
- ኖቬምበር 17 ቀን፣ 2 p.m. | Link to Register

ስለማመልከቻው ቴክኒካዊ ድጋፍ ለማግኘት፣ ድርጅቶች ከታች በተመለከቱት ቀናት በተለመዱት የስራ ሰዓቶች ወቅት ዙም በኩል ሰተት ብለው ብቅ ማለት መቀላቀል ይችላሉ። ቅድመ-ምዝገባ አስፈላጊ አይደለም።

- ኖቬምበር 29 ቀን፣ 10 a.m. – 11 a.m. | Link to Meeting
- ዲሴምበር 1 ቀን፣ 2 p.m. – 3 p.m. | Link to Meeting
- ዲሴምበር 6 ቀን፣ 3 p.m. – 5 p.m. | Link to Meeting

ያለቀጠሮ-ዱብ ብሎ የመገኘት የቢሮ ሰዓቶች የሚስተናገዱት በእንግሊዝኛ ነው። የቴክኒካዊ እርዳታን በእስፓኝ ወይም በሌላ ቋንቋ ለማመቻቸት፣ እባክዎ ለይናይትድ ዌይ በ foodsecurity@uwkc.org ኢ-ሜይል ያድርጉ።

## X. ተጨማሪ ጥያቄዎች

የማመልከቻ ሂደትን ለሚመለከቱ ጥያቄዎች፣ እባክዎ ዩናይትድ ዌይ ኦፍ ኪንግ ካውንቲን በ foodsecurity@uwkc.org ይገናኙ።

## XI. ማመልከቻ

የድርጅትዎን ማመልከቻ፣ እባክዎ በሚከተለው በሚከተለው አገናኝ በኩል በበይነ-መረብ መስመር (ኦንላይን) ያስገቡ: https://fightpoverty.formstack.com/forms/2021FSAP_application. ማመልከቻው፣ ረቡዕ ዕለት፣ ዲሴምበር 8 ቀን፣ 2021 ሳያልፍ መድረስ አለበት።

ምላሽዎን ወርድ ዶኪዩሜንት ፎርማት አሰናድተው ይህንኑ ኮፒ በማድረግ በበይነመረብ የመስመር ላይ ማመልካቻ ውስጥ እንዲለጥፉት እንመክራለን። ማመልከቻዎን እባክዎ የበይነመርቡን ቅጽ በመጠቀም ብቻ ያስገቡ። በኢሜል የሚላኩ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም። ማስገባትዎን የሚያረጋግጥ አውቶማቲክ የኢሜል መልእክት ይደርስዎታል።

በቋንቋ ወይም በቴክኒክ መሰናክሎች ምክንያት፣ የመስመር ላይ ማመልከቻን ለመሙላት እርዳታ ከፈለጉ፣ ምላሾችዎን በእንግሊዘኛ እስከ አርብ ዲሴምበር 3 ቀን ድረስ ለ foodsecurity@uwkc.org ማቅረብ ይችላሉ፣ እና የዩናይትድ ዌይ ሰራተኛ መረጃውን ወደ የመስመር ላይ ስርዓታችን ያስገባልዎታል።

ለማጣቀሻ ያክል፣ ማመልከቻው የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያካትታል:

**ክፍል 1: የብቁነት ማረጋገጫ**

**ክፍል 2:የኢጀንሲ ወይም ጥምረት/ቅንጅት መረጃ**

1. የድርጅት ስም
2. ድርጅትዎ የገንዘባዊ ጉዳዮች/ፊስካል ደጋፊ (ስፖንሰር) አለው? መልስዎ አዎ ከሆነ፣ እባክዎ የፊስካል ኤጀንቱን ስም ይስጡ።
3. ዋነኛ የግንኙነት ስም
4. ዋነኛ የኢ-ሜይል መገናኛ አድራሻ
5. ዋነኛ የስልክ ግንኙነት ቁጥር
6. ይህ ፕሮፖሳል ለተናጠል ድርጅት ነው ወይስ ለጥምረት/ቅንጅት?
   - ☐ ነጠላ ድርጅት

- ጥምረት/ቅንጅት

7. ጥምረት/ቅንጅት ከሆነ: የጠምረቱ አጋሮች ስም
8. ጥምረት/ቅንጅት ከሆነ: እባክዎ የእያንዳንዱን የጥምረቱ አባል ድርጅቶችን ዋነኛ ስሞች እና የኢ-ሜይል አድራሻዎች ይስጡ
9. የድርትጅት ወይም የጥምረት ተልዕኮ
10. ጥምረት/ቅንጅት ከሆነ: የጠምረት አጋርነታችሁ እንዴት እንደተዋቀረ ያግለጹ፣ ይህም የትኛው(የትኞቹ) ድርጅት(ቶች) የፊስካል ግንባር መስመረኛ(ኞች) እንደሚሆኑ፣ እና ቡድኑ የተመደበለትን የገንዘብ ድጎማ ለተመደቡት የፕሮግራም አጋሮች እንዴት እንደሚያደለድል ማብራራትን ይጨምራል።
11. ጥምረት/ቅንጅት ከሆነ: ጥምረቱ/ቅንጅቱ በአጋር ድርጅቶቹ መካከል የተደረገ የጽሁፍ ስምምነት በመዝገቡ ውስጥ ሊኖረው እንደሚገባ ተረድቻለሁ።
12. ድርጅትዎ፣ በአሁን ወቅት ላይ፣ በፌደራል የተፈቃጅ ድጎማ አስተዳደር (SAM.gov) ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኝ ነው? መልስዎ አዎ ከሆነ፣ የ SAM ምዝገባዎን የሚያሳይ የስክሪንሾት ያቅርቡ።

*ጠቃሚ ጊዜዎን እናከብራለን። ከታች ያሉትን ጥያቄዎች በመመለስ ወቅት፣ ሀሳቦችዎን በብቃት ለማራራት፣ እባክዎ በቂ ዝርዝሮችን ያቅርቡ፣ ነገርግን ማልሸዎን በተቻለ መጠን እጥር ምጥን ያድርጉ። ከዚህ ቀደም ለሌሎች ፕሮፖሳሎች ቀርበው የነበሩ ትርክቶች እዚህ አምጥተው ማዛመድ ይችላሉ።*

13. ለምግብ ማከፋፈያ ፕሮጀክት ያቀረቡትን ፕሮፖሳል በአጭሩ ይግለጹ። በማብራሪያዎ ውስጥም የሚከተሉትን ፤ያካትቱ: ለማሰራጨት ያቀዱት የምግብ አይነት፤ ምግቡ የት፤ ስንት ጊዜ፣ ምን ያህል፣ እና መቼ እንደሚከፋፈል፤ ምግቡን የሚያከፋፍለው ማን እንደሆነ፣ እና ለማገልገል ያሰቧቸው ህዝቦች፣ ማህበረሰቦች ወይም ስርዓቶች።
14. እጀንሲዎ ወይም ቅንጅትዎ፣ በዚህ ድጎማው በተመደበለት ፕሮጀክት፣ በጃንዋሪ 15 ቀን 2022 እና ኦክቶበር 31 ቀን፣ 2022 መካከል ባሉት ጊዚያት ውስጥ በድምሩ የቱን ያክል ተደጋጋሚ ግለሰቦችን ሊደርስ ይችላል? የተገመተውን ተደራሽነት እንዴት እንዳሰሉት እባክዎ በአጭሩ ያብራሩ።
15. ሊያገለግሏቸው ያሰቧቸው ማህበረሰቦች በኮቪድ-19 ምክንያት ያልተመጣጠነ ተጽዕኖ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ያደረባቸው እንዴት ነው? ወረርሽኙ ያስከተለባቸውን የተለዩ ዕያነት ፍላጎቶቻቸውን እንዴት ነው ማስተናገድ የሚችሉት?
16. ዩናይትድ ዌይ፣ በአነስተኛ-መሰናከል፣ ለተገሊጋይ ማህበረሰቦች ቀጣይነት ያለው የምግብ ተደራሽነትን ከሚያቀርቡ ድርጅቶች እና ጥምረቶች ጋር የኮንትራት ውል መዋዋል ያስባል። እባክዎን በአሁኑ ጊዜ በአነስተኛ-መሰናከል የምግብ አቅርቦት ተደራሽነትን እንዴት እንደሚያቀርቡ እና የኤጀንሲዎን የምግብ ፕሮግራም የተደራሽነ እንቅፋቶችን ለመቀነስ ያቀዱትን ማንኛውንም አዲስ ዕቅዶችዎን ያብራሩ።
17. ልታገለግሏቸው ያባችኋቸው ማህበረሰቦችን በመድረስ እና የምግብ አገልግሎቶችን በማቅረብ ሂደት ባደረጋችሁት ጉዞ፣ ድርጅትዎ ወይም ጥምረትዎ ያለውን ልምድ ይግለጹ። እባክዎ ለምግብ ዋስትና የዕገዛ ፕሮግራም አስፈላጊነት ያላቸውን ምሳሌዎች ይስጡ።
18. የተገልጋዩን ማህበረሰብ የባህላዊ ተቀባይነት ያልቸውን እና/ወይም የተለዩ አመጋገብ የሚያስፈልጋቸውን በመረዳት ረገድ፣ ድርጅትዎ/ኤጀንሲዎ ከተገልጋዩ ማህበረሰብ ጋር እንዴት ሊሻረክ (አጋርነት ሊፈጠር) ይችላል? በዚህ የፕሮጀክት ዘመን ውስጥ ሳሉ፣ የማህበረሰቡን ግብረ-መልስ እንዴት እንደሚያነቃቁ እና እንዴትስ ምላሽ እንደሚሰጡ ይግለጹ።
19. ድርጅትዎ/ኤጀንሲዎ የምግብ እደላ ማከናወንን ለማስቻል ያሉትን ግብዓቶች (ለምሳሌ፣ ተቀማጭ መጠባበቂያ በጥሬ ገንዘብ (ካሽ)፣ ሰራተኞች፣ የምግብ ማከማቻ መጋዘን እና ማጓጓዣ፣ አስተማማኝ ሽርክና፣ እና አከፋፋዮች) ያሉት መሆኑን ይግለጹ።
20. የፌደራል ተደጓሚ ገንዘን በማስተዳደር ረገድ ያለዎትን ልምድ ይግለጹ። ይህ የፌደራል ተደጓሚ ገንዘብን የማስተዳደር ልምድ ከሌለዎት፣ የከተማ፣ የካውንቲ፣ ወይም ክፍለ-ሀገር (ስቴት) ገንዘብ ዳረጎቶችን የማስተዳደር ልምድዎን ይግለጹ።

የተፈቀደው ዳረጎት (ግራንት) በሚጠይቀው መሰረት፣ ወጪዎችን፣ ሪፖርት አቀራረቦችን፣ እና የሰነድ አጠባበቆችን እንዴት እንደሚይዙ ይግለጹ።

21. ማጋራት የሚፈልጉት ሌላ ተጨማሪ ነገር አለዎት?

**ክፍል 4: የስነህዝብ መረጃ/ዳታ**

22. እርስዎ በደንብ እስከሚያውቁት ድረስ፣ እባክዎ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የእርስዎን ድርጅት ወይም የቅንጅትዎን የምግብ ፕሮግራሞች ሊደርሱ ስለቻሉ ደንበኞችዎ የህዝብ የስነህዝብ መረጃ/ውሂብ ያጋሩ። እንደ ጥምረት በትብብር የምትሰሩ ከሆነ፣ እባክዎ አጠቃላይ ድምር ለፕሮግራሞቻችሁ አቅርቡ። ለተጠቀሰው መስክ የደንበኛ መረጃ/ውሂብ ካልሰበሰቡ፣ እባክዎን "unknown"/ "ያልታወቀ" ብለው ይፃፉ።
    - ☐ ልጆች (18 ዓመት እና በታች)
    - ☐ ወጣት ጎልማሶች (18 እስከ 24 ዓመት ዕድሜ)
    - ☐ LGBTQ+
    - ☐ ቋሚ መኖሪያ የሌለው/ቤት አልባ
    - ☐ አዛውንት (60 ዓመት እና በላይ)
23. እርስዎ በደንብ እስከሚያውቁት ድረስ፣ እባክዎ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የእርስዎን ድርጅት ወይም የቅንጅትዎን የምግብ ፕሮግራሞች ሊደርሱ ስለቻሉ ደንበኞችዎ የህዝብ የስነህዝብ መረጃ/ውሂብ ያጋሩ። እንደ ጥምረት በትብብር የምትሰሩ ከሆነ፣ እባክዎ አጠቃላይ ድምር ለፕሮግራሞቻችሁ አቅርቡ። ለተጠቀሰው መስክ የደንበኛ መረጃ/ውሂብ ካልሰበሰቡ፣ እባክዎን "unknown"/ "ያልታወቀ" ብለው ይፃፉ።
    - ☐ አፍሪካዊ ስዱድ-ገብ
    - ☐ አፍሪካዊ-አሜሪካዊ/ጥቁር
    - ☐ አሜሪካዊ ህንድ /የአላስካ ተወላጅ
    - ☐ እሲያዊ (ቻይናዊ፣ ጃፓናዊ፣ ኮሪያዊ፣ ወዘተ.)
    - ☐ የደቡባዊ እሲያ ሰው (ህንዳዊ፣ ፓኪስታናዊ፣ ቤጋላዊ፣ ወዘተ.)
    - ☐ የደቡብ ምስራቅ እሲያ ሰው (ታይ፣ ሉ ሚይናዊ፣ ሆሞንጋዊ፣ ቪዬትናማዊ፣ ካምቦዲያዊ፣ ወዘተ)
    - ☐ ላቲናዊ
    - ☐ የሃዋይ ተወላጅ /የፓሲፊክ ደሴት ሰው
    - ☐ የመካከለኛው ምስራቅ ሰው (ኢራቃዊ፣ ኢራናዊ፣ ሳዑዲ አረቢያዊ፣ ቱርካዊ፣ ወዘተ.)
    - ☐ ኮውኬዢያዊ/ነጭ/መሰረተ አውሮጳዊ
    - ☐ ባለብዙሃ-ዝርያ
    - ☐ ያልታወቀ

**ክፍል 5: ባጀት**

24. የተጠየቀው የገንዘብ መጠን
25. እባክዎ ከታች ያለውን የባጀት ቴምፕሌት/ቅጽ ይሙሉ፣ እናም ከምግብ ዋስትና የዕገዛ ፕሮግራም ለተጠዬቀው የገንዘብ ድጎማ፣ እርስዎ ለማውጣት ያቀዱትን ወጪዎን ይዘርዝሩ። ከተፈቀደው/በዳረጎትነት ከተሰጠው ገንዘብ ቢያንስ 75%ቱ ምግብን የመግዛት አገልግሎት ላይ መዋል አለበት። ከተፈቀደው ገንዘብ ውስጥ ከ25% የማይበልጠው ገንዘብ፣ ለደሞዞች፣ ለጥቅማጥቅሞች፣ ለአቅርቦቶች፣ እና ቀጥተኛ ላልሆኑ ወጪዎች ሊመደብ ይችላል።
    - ☐ ምግብ
    - ☐ ድምወዞች እና ምንዳዎች
    - ☐ ተጓዳኝ ጥቅማጥቅሞች
    - ☐ ጉዞ
    - ☐ አቅርቦቶች

- ቦታ (ክራይ፣ ንብረትን የጠቀም ክፍያዎች፣ ወዘተ.)
- የገበያ ማስታወቂያ እና በረዥሙ መድረስ
- ቀጥተኛ ያልሆነ ክፍያ